## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 234865
ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- አቶ ሁሴን መሐመድ አሊ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ መሠረት አበበ መኮንን

2. ነጻነት ታምሩ በሻህ

} የቀረበ የለም

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መሥከረም 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 130358 ሕዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 283153 ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማን ይዞታን በሚመለከት የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በቦሌ ክፍለከተማ ወረዳ 12 ውስጥ የሚገኝ በሰሜን ከአቶ ዩናስ ስለሺ፤ በደቡብ ከአቶ ማሩ ገ/ዩሀንስ፤ በምስራቅ 15 ሜትር እና በስተምዕራብ ከ1ኛ ተጠሪ በኋላም ይዞታው ከተዛወረላቸው 2ኛ ተጠሪ ጋር የሚዋሰን 150

ካ.ሜ ይዞታ እና ቤት የካቲት 12 ቀን 2011 ዓ.ም በተፈጸመ የሽያጭ ውል ገዝቻለሁ፤ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በ2ኛ ተጠሪ ስም ከተዛወረው 400 ካ.ሜ ይዞታ በጋራ በምንዋሰንበት በኩል ያለውን ተጠሪዎች 3.50 ሜ በ 10 ሜትር በአጠቃላይ 35 ካ.ሜ ከሠኔ 29 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሀይል ወደ ይዞታቸው አካተው ሕገወጥ ግንባታ ገንብተዋል፤ ስለሆነም የፈጠሩት ሁከት ተወግዶ ግንባታውን አቁመው ይዞታውን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው ስላልቀረቡ መብታቸው ታልፎ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

2ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በሕጋዊ መንገድ ነሐሴ 14 ቀን 2012 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ሽያጭ ውል 400 ካ.ሜ የሆነ መኖሪያ ቤት ግዝቼ የሊዝ የባለይዞታ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶኛል፤ ከሚመለከተው አካል ሕጋዊ የግንባታ ፈቃድ በማውጣትም ግንባታ ጀምሬለሁ፤ የአመልካች ይዞታ 150 ካ.ሜ ሲሆን የ2ኛ ተጠሪ ደግሞ 400 ካ.ሜ ነው፤ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪዎች በአመልካች ይዞታ ላይ የሁከት ተግባር ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ስለይዞታው አጣርቶ ምላሽ እንዲልክ የታዘዘው የቦሌ ክፍለከተማ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በመመልከት በካርታ የተጠቀሰውን 150 ካ.ሜ አመልካች ይዘው እንደሚገኙ፤ የግንባታ ፈቃድ አውጥተውም ግንባታ በመገንባት ላይ መሆናቸውን፤ 2ኛ ተጠሪም በግዢ ባገኙት ካርታ መሠረት በካርታቸው ከተጠቀሰው 400 ካ.ሜ አልፈው አስፋፍተው ወደ መንገድ መያዛቸውን፤ ሆኖም አስፋፍተው የያዙት አመልካች ክስ ባቀረቡበት የክርክሩ ይዞታ በኩል አለመሆኑን፤ በምልከታው ወቅት የግራቀኙ ተወካዮች በቦታው መኖራቸውን እና መፈረማቸውን በመግለጽ ምላሽ ልኳል፤ ተጠሪዎች ወደ አመልካች ይዞታ በመግባት እንዳይጠቀሙበት መሰናክል ያልፈጠሩ በመሆኑ የፈጠሩት የሁከት ተግባር የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አስተዳደሩ በላከው ምላሽ ላይ ግራቀኙ አስተያየት ሰጥተዋል፤ አመልካች ደብዳቤው ማሕተም የለውም የሚል አስተያየት በስር ፍርድ ቤት አላቀረቡም፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መዝገቡ ላይ የተያያዘው ደብዳቤ ማሕተም ያረፈበት ስለመሆኑም አረጋግጧል፤ የመሬት ይዞታ ባለሙያው ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በመገኘት ተገቢውን ልኬት በመውሰድ አጣርቷል፤ አስተዳደሩ ማስረጃውን ሲያጣራ እንዴት አድርጎ ማጣራት እንዳለበት በችሎቱ በተለየ መንገድ እንዲያጣራ ትዕዛዝ እስካልተሰጠው ድረስ መንግስት ባወጣው መመሪያ እና የውስጥ የዳበረ አሰራር መሠረት ስራውን ሰርቶ ማስረጃውን ለፍርድ ቤቱ እንደላከ ይታመናል፤ አስተዳደሩ እስኬች እንዲልክ ስላልተጠየቀ ይህን አለመላኩ አያስነቅፈውም፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቶታል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች መሥከረም 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት ማስረጃው እንዲቀርብልኝ ጥያቄ አቅርቤአለሁ፤ ተጠሪዎች ያለአግባብ የአመልካችን ይዞታ መያዛቸው ከአስተዳደሩ በቃል ተነግሮኛል፤ ለፍርድ ቤቱ ክስ ከማቅረቤ በፊት ባለሙያው ለመስሪያ ቤቱ በጽሑፍ ሪፖርት ስለማቅረቡም ሆነ ከማሕደሬ ውስጥ ማስረጃው ስለመያያዙ አላውቅም፤ በቃል ከተነገረኝ ውጪ ለፍርድ ቤቱ ምላሽ እንደተሰጠ ቀርቤ ስጠይቅ ባለሙያው ቀደም ሲል ሐምሌ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ለመስሪያ ቤቱ በጽሑፍ ሪፖርት እንዳቀረበ ለማወቅ የቻልሁ መሆኑን በመግለጽ ያቀረብኩት የተጨማሪ ማስረጃ ይያያዝልኝ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፤ ፍርድ ቤቱ አስተዳደሩ ያላግባብ የሰጠውን መልስ መሠረት በማድረግ የአመልካችን የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ እና ምስክሮች ሳይሰሙ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት ከቦሌ ክፍለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት የይዞታ አስተዳደር ተጠይቆ እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃ ሳያስቀርብ የወሰነበት አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪ በአዲስዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

2ኛ ተጠሪ ጥር 23 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ ግንባታ የፈጸምኩት በራሴ ይዞታ ላይ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፤ የአመልካች ይዞታም በባለሙያ ተለክቶ 150 ካ.ሜ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች ከዚህ ቀደም በባለሙያ ተጣርቶ በቃል ተነግሮኛል ካሉት ውጪ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያያዝላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት የለም፤ አመልካች ራሳቸው በባለሙያ ተጣርቶ የልኬት ውጤት እንዲመጣ በስር ፍርድ ቤት ጠይቀዋል፤ ጉዳዩም በሚመለከተው የአስተዳደር አካል በአግባቡ ተጣርቷል፤ የተሰጠው ምላሽም ማሕተም ያለበት ነው፤ ስለሆነም ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ ይዘት መረዳት እንደቻልነው አመልካች ተጠሪዎቹ ይዞታቸውን አልፈው እንደያዙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሠረት ከቦሌ ክፍለከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት የይዞታ አስተዳደር ይጠየቅልኝ ማለታቸውን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቦሌ ክፍለከተማ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በሚመለከት ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታቸው ከሚያመለክተው ይዞታ አልፈው ወደ አመልካች ይዞታ መግባት ያለመግባታቸውን፤ ገብተዋል ከተባለ ምን ያህል ካ.ሜ ይዞታ አልፈው እንደገቡ በማጣራት ምላሽ እንዲልክ ያደረገ መሆኑን፤ ይህንኑ ምላሽ መሠረት በማድረግም ተጠሪዎች የፈጸሙት የሁከት ተግባር የለም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፤ በሌላ በኩል አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች አልፈው ይዞታዬን እንደያዙ በቃል የተነገረኝ ሲሆን ይኸው በጽሑፍ እንደቀረበ እና ማስረጃው ከማሕደሬ ጋር ተያይዞ እንደሚገኝ በወቅቱ ያልተነገረኝ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቱን ማስረጃውን እንዲያስቀርብልኝ ጠይቄ ተጠሪዎች አስተያየት ሳይሰጡበት በቂ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ባልሆነ ምክንያት ውድቅ የተደረገ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዲያስቀርብልኝ ብለው መጠየቃቸውን፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበው ጥያቄ በይግባኝ ቅሬታቸውም ላይ የገለጹት በመሆኑ በቀረበው ቅሬታ መሠረት ተመርምሮ ትዕዛዝ የሚሰጥ እንጂ በአቤቱታ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ ያደረገው እና ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ያጸናው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ለማስረዳት ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ፤ በእጃቸው የማይገኙትን ማስረጃዎች ደግሞ ማስረጃዎቹ ካሉበት ቦታ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲቀርቡላቸው መጠየቅ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222፤ 223፤ 234 እና 145 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ የማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ስርዓትም በህጉ በተመለከተው አግባብ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በቃል ተሰምቶና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247፣ 248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ ለጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡት የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ተሰምተውና አስፈላጊ ሲሆንም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ በማድረግ ጉዳዩን በሚገባ አጣርቶ እውነትን መሰረት ያደረገ ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑን በሕግ አግባብ የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት፣ ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን በማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይችል ስለማስረጃ አቀባበል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138፣ 257፣ 258 እና 259 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤ የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የሕጉ አገላለጽ የሚያስረዳ ሲሆን ይህ የማስረጃ አቀባበል አካሄድ ፍርድ ቤቱ በፍርድ አፃፃፍ ወቅት የግድ ሊከተለው የሚገባው መሆኑን የድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በዋነኝነት የሚከራከሩት ተጠሪዎች ያለአግባብ የአመልካችን ይዞታ መያዛቸው ከአስተዳደሩ በቃል ተነግሮኛል፤ ለፍርድ ቤቱ ክስ ከማቅረቤ በፊት ባለሙያው ለመስሪያ ቤቱ በጽሑፍ ሪፖርት ስለማቅረቡም ሆነ ከማሕደሬ ውስጥ ማስረጃው ስለመያያዙ አላውቅም፤ ባለሙያው ቀደም ሲል ለመስሪያ ቤቱ በጽሑፍ ሪፖርት እንዳቀረበ ለማወቅ የቻልሁ መሆኑን በመግለጽ ያቀረብኩት የተጨማሪ ማስረጃ ይያያዝልኝ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡

አመልካች በዚህ አግባብ የሚከራከሩ ቢሆንም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቦሌ ክፍለከተማ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በሚመለከት ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታቸው ከሚያመለክተው ይዞታ አልፈው ወደ አመልካች ይዞታ መግባት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያለመግባታቸውን፤ ገብተዋል ከተባለ ምን ያህል ካ.ሜ ይዞታ አልፈው እንደገቡ በማጣራት ምላሽ እንዲልክለት አድርጓል፤ ተጠቃሹ አካልም ለፍርድ ቤቱ በሰጠው ምለሽ 2ኛ ተጠሪ በግዢ ባገኙት ካርታ መሠረት በካርታቸው ከተጠቀሰው 400 ካ.ሜ አልፈው አስፋፍተው ወደ መንገድ ከመያዛቸው በቀር አስፋፍተው የያዙት ይዞታ አመልካች ክስ ባቀረቡበት የክርክሩ ይዞታ በኩል አለመሆኑን ገልጿል፤ አመልካች በማሕደሬ ውስጥ ይገኛል የሚሉት የተጨማሪ ማስረጃ ይቅረብልኝ አቤቱታም በስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመርምሮ ክሱን ባቀረቡበት ወቅት ያላቀረቡት በከባድ እና በቂ በሆነ ምክንያት ባለመሆኑ እንዲሁም ባለሙያው ይዞታውን አይቶ 35 ካ.ሜ ተገፍቷል ብሎ ነግሮኛል በሚል ያቀረቡ ቢሆንም ስለጉዳዩ የሚመለከተው አካል ልኬት አድርጎ ምላሽ የሰጠ በመሆኑ እና አስፈላጊውን ማስረጃዎች ፍርድ ቤቱ ያስቀረበ በመሆኑ የተጨማሪ ማስረጃ ይያያዝልኝ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው ስለመሆኑ ይህ ችሎት በትዕዛዝ ያስቀረበው የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከአስተዳደሩ የቀረበው ምላሽ ተገቢው የተቋም ማሕተም ያረፈበት መሆኑን፤ የመሬት ይዞታ ባለሙያው ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በመገኘት ተገቢውን ልኬት በመውሰድ ተገፍቶ የተያዘ የአመልካች ይዞታ አለመኖሩን ያጣራ መሆኑን አረጋግጦ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቶታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10/1 ላይ እንደተመለከተውም አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በማለት ሊታረም የሚችለው የተሰጠው ውሳኔ የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን ከሆነ፤ ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ የሚጠቅስ ከሆነ፤ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ ከተወሰነ፤ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ ከተወሰነ፤ በፍርድ አፈጻጸም ሒደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ ከተሰጠ፤ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ሳይኖር ከተወሰነ፤ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከሕግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ ከሆነ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎቹ ይዞታዬን ገፍተው በመግባት ሕገወጥ ግንባታ ገንብተዋል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በካርታ የተጠቀሰውን 150 ካ.ሜ ይዞታቸውን ይዘው እንደሚገኙ፤ 2ኛ ተጠሪም በግዢ ባገኙት ካርታ መሠረት በካርታቸው ከተጠቀሰው 400 ካ.ሜ አልፈው አስፋፍተው ወደ መንገድ ከመያዛቸው በቀር አስፋፍተው የያዙት የአመልካች ይዞታ እንደሌለ ተረጋግጦ ተጠሪዎች የፈጠሩት የሁከት ተግባር የለም በማለት ተወስኗል፡፡ በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ በአብዛኛው ከፍሬነገር ክርክር እና ከማስረጃ ምዘና

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10/1(ለ) በተመለከተው የመሠረታዊ የሕግ ስሕተት መመመዘኛ መሠረት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ እንደመረመርነው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 130358 ሕዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 283153 ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትዕዛዝ

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 130358 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም